# ማመልከቻ፤

ይድረስ፤ ለእርስዎ ለውድ አንባቢዬ፣
ጉዳይ፤ የሀገር አንገብጋቢና አሳሳቢ ሁኔታ
ቀን፤ እሁድ፤ ግንቦት ፲፮ ቀን፤ ፳፻፯ ዓመተ ምህረት ( 5/24/2015 )

## ውድ ኢትዮጵያዊያ፤

እርስዎ ለሀገርዎና ለወገንዎ፤ ሌት ተቀን ያለመታከት እስከዛሬ ያደረጉትን አስተዋፅዖ አደንቃለሁ። ሀቁ ደግሞ፤ ያ አልበቃ ብሎ፤ አሁን ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ እኔ ለርስዎ የምተርከው አይደለም። እያንዳንዳችን ማድረግ ያለብንን በሚመለከትም፤ ለቀባሪው ማርዳት ስለሆነ፤ በቀጥታ ይኼን ለርስዎ እንድጽፍ ወደ ተገደድኩበት ጉዳይ እገባለሁ።

ሀገራችን የጋራችን ናት። ተደራጀንም አልተደራጀንም ይኼ አይለወጥም። ስለዚህ የሀገር ኃላፊነቱ የያንዳንዳችን ነው። በሀገራችን በኢትዮጵያ ያለው የፖለቲካ ሀቅ፤ በየድርጅቶች ተኮልኩለን የምንታገልበት ሳይሆን፤ በአንድነት ተሰባሰበን መነሳት ያለብን ግዴታ ነው። የመሰባሰቡን ጉዳይ ካነሳሁ ዘንዳ፤ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች አስፈላጊነቱን አምነው፤ ጥሪዎችን በተደጋጋሚ አስተላልፈዋል። ይኼን በመደገፍ ባለፉት ሁለት ቀኖች፤ የመሰባሰቡ ጉዳይ ዋና አጀንዳ እንዲሆን፤ ጥረት ጀመርኩ። እስከዛሬ ከተደረጉት ሙከራዎች የተለዬ ሙጫ ሃሳብ ይዤ አይደለም። ከተለያዩ ግለሰቦች በጣም አበረታታች መልሶች ተላኩልኝ። በጣም አመሰግናለሁ። ከአንድ ድርጅት ጊዜያዊ አሰባሳቢ ሙሉ ድጋፍ አገኘሁ። አነጋጋሪ ሰዎችም ሊመድቡልኝ ለዛሬ፤ እሁድ፤ ግንቦት ፯ ቀን፤ ፳፻፯ ዓመተ ምህረት፤ ቀጠሮ ይዣለሁ። በተጨማሪም ከግል ይልቅ በስብስብ የማሰባሰቡን ኃላፊነት መውሰዱ ይሻላል በማለት ከጋበዝኳቸው ሰዎች፤ ከፊሎቹ በፈቃደኝነት መልስ ልከውልኛል። እኔ ተጋባዥዎችንም ሆነ አጀንዳውን አንጠልጥዬ አልቀረብኩም። በምኅዳሩ ላይ ያለውን ሀቅ ተቀብዬ ነው ማሰባሰቡን የጀመሩኩ። የተጠቀሱትን ድርጅት መሪዎች በግል ስለምወዳቸው ወይንም የተለዬ ግንኙነት ስላለኝ አይደለም። ጥሩዎች ናቸው፣ ጥሩ ታሪክ አላቸው፣ ያደርጉታል፣ ወይንም ምኞቴ ከተጨባጩ እውነታ ስለራቀ አይደለም። የት ልጀምር በሚለው ተመርቼና ሀቁን ተቀብዬ ነው። እንግዲህ እዚህ ላይ ነው እርስዎ የሚመጡት።

እኔ ይህ የማሰባሰቡ ጉዳይ ይሳካል ወይም አይሳካም፤ ከሚለው አይደለም የምነሳው። የምነሳው አሁን ሁላችን ምን ያስፈልጋል እያልን ነው? እምነታችንስ ምንድን ነው? ከሚለው ነው። ይህ ትግል በአንድ ድርጅት ተካሂዶ ቢከናወን የትግል እምቡዋለሌ ነው። በተጨማሪም በድርጅቶች ውስጥ ካሉት ይልቅ፤ በግለሰብ ከፍተኛ ጥረት በማድረግና የትግል ፍላጎቱ ያላቸው ቁጥር እጅግ የላቀ ነው። ታዲያ ይሄ ሁሉ በትግል ጎራው ባለበት ወቅት፤ እንዴት ትግሉ ባለበት ይረግጣል?

በኔ እምነት፤ በውጭ ሀገር ያለነው ኢትዮጵዊያን፤ ሀገር አቀፍ የሆነ አንድ ኢትዮጵያዊ ሕዝባዊ ንቅናቄ መሥርተን ብንነሳ፤ ለትግሉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እናደርጋለን። አነሳሴም ከዚህ ነው። በኔ እምነት፤ ይህ ትግል የድርጅቶች ትግል አይደለም። ይህ ትግል የሁላችን ሀገር አድን ትግል ነው። ሀገር አድን ትግሉ ደግሞ የሚካሄደው፤ ኢትዮጵያዊያን በአንድነት ተነስተን እንጂ፤ በዚህ ወይንም በዚያ ድርጅት በተናጠል አይደለም። ስኬቱም አስተማማኝ የሚሆነው በዚህ መንገድ ስንሄድ ነው።

ታዲያ መሰባሰቡን ለምን በድርጅቶች ላይ ብቻ እጥለዋለሁ? እርስዎ ከማን ያነሰ ኢትዮጵያዊነትና ለሀገርና ወገን መቆርቆር አለዎ?

ከድርጅቶችም ሆነ ከግለሰቦች “መሰባሰቡን እንፈልጋለን!” ማለቱ ብቻ በቂ አይደለም። ለመሰባሰቡ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል። እናም እርስዎን ጥረት እንዲያደርጉ እየጠየቅሁ ነው። አዳምጠውኛል? እርስዎን ነው!

ለሀገር አድን መሰባሰብ ብዙ አይጠይቅም። መሰባሰቢያ ነጥቦቹም ብዙ አይደሉም። ታዲያ ከዚህ ያነስ፤ ኢትዮጵያ ከርስዎ ምን ትጠይቅ? መልስዎትን እጠብቃለሁ። eske.meche@yahoo.com http://nigatu.wordpress.com

ከታላቅ ምስጋና ጋር
አንዱዓለም ተፈራ